# LITURGIA,

SEU

# LIBER PRECUM COMMUNIUM,

ET

## Administrationis Sacramentorum,

ALIORUMQUE RITUUM ET CÆREMONIARUM

IN

ECCLESIA ANGLICANA ET HIBERNICA

RECEPTUS;

CUM EPISTOLARUM ET EVANGELIORUM PERICOPIS,

ET EORUM COLLECTIONIBUS;

AC

LIBRO PSALMORUM:

ITEM,

FORMA ET MODUS CREANDI, ORDINANDI, ET CONSECRANDI EPISCOPOS, PRESBYTEROS, ET DIACONOS.

*AMHARICÈ VERSUS*

CAROLO GULIELMO ISENBERG.

LONDINI:

IMPRESSIT RICARDUS WATTS,

IMPENSIS SOCIETATIS AD COGNITIONEM CHRISTIANAM EVULGANDAM INSTITUTÆ.

M DCCC XLII.

# የጉባኤ ፡ ጸሎት ፡

የምሥጢራትም ፡ ማገልገል ፡

የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የቀረች ፡ ሥርዓተዋ ፡

በተዋህደች ፡

በእንግሊጣርና ፡ በኢርላንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

እንደሚደረግ ፡

ከዳዊት ፡ መዝሙራት ፡ መጽሐፍ ፡ ጋራ ፡

ባብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንደሚደገሙ ፡

ተከፍሎ ።

በቻርልስ ፡ ዊልየም ፡ ኢዘንበርግ ፡

በወንጌል ፡ መልእክተኛ ፡

ባምኃርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተተረጐመች ፡

በሎንደንም ፡ በእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ከተማ ፡ የክርስ
ቲያንንም ፡ እውቀት ፡ ለመዝረጋት ፡ ባበረች ፡ ጉባኤ ፡
በፈቃድዋ ፡ በሪቻርድ ፡ ወትስ ፡ ማኅተምያ ፡ ታተመች ፡
በክርስቶስ ፡ ልደት ፡ አመት ፡

፲፰፻፴፬።

## በሐበሻ ፡ ላሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡፡

ጸጋ ፡ ይሁንላችሁ ፡ ሰላምም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዘንድ ፡ ከጌታችንም ፡ ከየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡

ይህች ፡ መጽሐፍ ፡ በጃችሁ ፡ ትሰጣችኋለች ፡ ፀብንና ፡ ክርክርን ፡ ለማስነሣት ፡ አይደለም ፡ እላንትም ፡ ሥርዓታች ሁን ፡ ትታችሁ ፡ የኛን ፡ ሥርዓት ፡ ትከተሉ ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ፡ በፍቅር ፡ እንጅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ በእንግልጣርና ፡ በኢርላንድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ላለች ፡ ለክርስቲያን ፡ ሕይወት ፡ በሃይማኖትና ፡ በትምህርት ፡ በሕይወትም ፡ ምስክር ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡፡ የፍቅርን ፡ እጃችን ፡ ወደላንት ፡ ዘርግተን ፡ የጳውሎስን ፡ ነገር ፡ እንላችኋለን ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ ሁሉን ፡ መርምሩ ፡ በጎንም ፡ ጠብቁ ፡፡

## በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የሚገኝ ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡


፩፡ መቅደም ፡፡
፪፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ማገልገል ፡፡
፫፡ ስለ ፡ ማምለክ ፡ ሜዳዊ ፡ ነገር ፡፡
፬፡ ስለ ፡ መዝሙራት ፡ ንባብ ፡፡
፭፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ንባብ ፡፡
፮፡ በእሁድና ፡ በበዓል ፡ ሁሉ ፡ የሚነበብ ፡ የንባብ ፡ ታቡላ ፡፡
፯፡ ከለንደርዩም ፡፡
፰፡ የጽዋት ፡ ጸሎት ፡፡
፱፡ የማታ ፡ ጸሎት ፡፡
፲፡ የአተናቴዎስ ፡ ስምቦሎን ፡፡
፲፩፡ ሊጣንያ ፡፡
፲፪፡ ለመናና ፡ ምስጋና ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜያት ፡፡
፲፫፡ ለመኖች ፡ የመልእክትና ፡ የወንጌልም ፡ ክፍሎች ፡፡
፲፬፡ የቍርባን ፡ ሥርዓት ፡፡
፲፭፡ የጥምቀት ፡ ሥርዓት ፡፡
፲፮፡ ከተኪስሞስ ፡፡
፲፯፡ ማጽናት ፡፡
፲፰፡ መጋባት ፡፡
፲፱፡ ገንዘት ፡፡
፳፡ የዳዊት ፡ መዝሙራት ፡፡
፳፩፡ ቅያሜ ፡፡
፳፪፡ ፻፱፡ ቃላት ፡፡
፳፫፡ የዝምድና ፡ ታቡላ ፡፡
፳፬፡ የጳጳሳት ፡ የቀሳውስትም ፡ የዲያቆናትም ፡ ቅደሴ ፡፡

# መቅደም ፡፡

የእንግልጣር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የግልጽ ፡ ማምለክዋ ፡
ሥርዓት ፡ ከተሠራች ፡ ጀምሮ ፡ ለዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ከሁለት ፡ ጫሬሽ ፡ ተግድፎቶች ፡ በመካከል ፡ ያለውን ፡ እ
ውነተኛውን ፡ መንገድ ፡ ይዛ ፡ ከዚች ፡ ሥርዓት ፡ መለየት ፡
ሲገባ ፡ ጊዜ ፡ እምቢ ፡ እንዳትል ፡ ሳይገባም ፡ ለመለየት ፡ ቀ
ሊል ፡ አድርጋ ፡ እሺ ፡ እንዳትለው ፡ ወትሮ ፡ ትጠነቀቅ ፡ ዘ
ንድ ፡ ጥበብ ፡ ነከረችላት ፡፡ ባንድ ፡ እጅ ፡ ለደህና ፡ መክንያ
ት ፡ የተሰራ ፡ ነገር ፡ በግድ ፡ መለወጥ ፡ ሳይሻ ፡ በተለወጠ ፡
ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ መለወጥ ፡ እርሱን ፡ ለማሻል ፡ ከተደረገለት ፡
ከቀደመው ፡ ግድፈት ፡ የሚከፋ ፡ ነገር ፡ እንዲነሣ ፡ ዕለት ፡
ዕለት ፡ የሚሆን ፡ ነገር ፡ ይገልጻልና ፡፡ እንዲሁም ፡ በሁለተኛ ፡
እጅ ፡ የማምለክ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሜደዊ ፡ መልክና ፡ ሥርዓት ፡
ለራሱ ፡ ምንም ፡ አይልምና ፡ ይህም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ታውቋልና ፡ ደህናና ፡ ከቢድ ፡ መክንያት ፡ ቢሆን ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡
ልዩ ፡ ጊዜና ፡ ስፍራ ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ መለወጥ ፡ የሚፈለ
ግበት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥልጣን ፡ ያለቻቸው ፡ ደህና ፡
እንደ መስላቸው ፡ እንዲለውጡት ፡ ይገባል ፡፡ ስለዚህም ፡
እናገኛለን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስ ፡ ወዲህ ፡ በአያ
ሌ ፡ ደህና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ባረፉ ፡ ነገሥታት ፡ በዘመናቸው ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ደህናና ፡ ከቢድ ፡ መክንያት ፡ በል
ዩ ፡ ልዩ ፡ በሥርዓት ፡ ነገር ፡ በየዘመናቸው ፡ መለወጥ ፡ እን
ዲሻ ፡ በመሰላት ፡ እሺ ፡ እንደለች ፡ ደሮ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ በሥርዓት ፡ ባሕሪና ፡ መልክ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡
እርሱ ፡ ሁኖ ፡ ቀረ ፡ ሲጸና ፡ ሳይለወጥም ፡ ወትሮ ፡ መለወጥ
ን ፡ የሚሹ ፡ የልባቸውንም ፡ ፈቃድ ፡ ከጉባዔ ፡ ጥቃሜ ፡ ይ
ልቅ ፡ የሚከተሉ ፡ ሰዎች ፡ ሳይታጡ ፡፡

ችንም : እንደ : ችሎታችን : ለሰው : ልብ : ሁሉ : እንገልጽ :
ዘንድ : ከተጋደልነ : በኋላ : ለሰው : ሁሉ : ደስ : ማሰኘት :
ሳይቻለን : (ምቀኞች : ከርሳቸው : ሌላ : ሰው : ያደረገ : ደህ
ና : መሆን : አይችልም : ይላሉ : እንጅ) : እኛ : ከዚህ : የም
ንሰጠው : ከሁለት : ግዛት : ጉባኤዎችም : በጣም : ተመር
ምሮ : ደህና : እንደ : ሆነ : የተገኘ : የእንግልጣር : ቤተ : ክ
ርስቲያን : ገሮች : ዕርቅንም : የሚወዱ : በውነትም : እግዚ
አብሔርን : የሚፈሩ : ልጆችዋ : በደህና : እንዲቀበሉት : ደ
ህና : ሁኖም : እንዲያገኙት : ተስፋ : እናደርጋለን ::

---

## በቤት : ክርስቲያን : ስለ : ማገልገል ::

በሰው : ብልሃት : ምንም : ከቶ : መልካም : አልተሠራ
ም : በምንትም : አልተተከለም : ዘመን : ሲያልፍ : ጊዜ :
ያልተጉደ : ከሌላ : ነገር : በቀር : ማምለክ : የሚባል : በ
ቤተ : ክርስቲያን : በግልጽ : በሚደረጉ : ጸሎቶች : እንደ
ሚታይ :: የቤተ : ክርስቲያንን : ማምለክ : መጀመርያው
ንና : መሠረቱን : ሰው : በቀደሙ : አባቶች : ዘንድ : ቢመ
ረምር : ለደህና : መክንያተ : ብቻ : ለአምልኮም : ጥቀሜ :
እንደ : ተሠራ : ያገኛል :: ያባቶች : ሥርዓት : እንደህ : ነበረ
ና : መጽሐፍ : ቅዱስ : ሁሉ : ወይስ : ታላቅ : ክፍሉ : ባመ
ት : ባመት : አንድ : ጊዜ : ይደገም : ዘንድ :: የዚህም : መ
ክንያታቸው : ቀሳውስት : ከሌሎችም : ይልቅ : ሳሙነኛ
ች : ብዙ : ጊዜ : አንብበው : በእግዚአብሔር : ቃልም : አ
ስበው : ነፍሳቸውን : ለእግዚአብሔር : ፍርሃት : ያነቁ : ዘ
ንድ : ሌሎችንም : በደህና : ትምህርት : ለመምከር : የውነ
ትንም : ጸላቶች : ለማሸነፍ : የተዘጋጁ : ይሆኑ : ዘንድ : ጉ
ባኤም : የመጽሐፍ : ቅዱስን : መነበብ : በቤተ : ክርስቲያ
ን : ዕለት : ዕለት : ሰምተው : አዘውትረው : በእግዚአብ
ሔር : ዕውቀት : ያድጉ : ዘንድ : እውነተኛውንም : ማምለ
ኩን : በመውደድ : ኢየበዙ : ይቃጠሉ : ዘንድ ::
ደሮ : ይህች : የድሮ : አባቶች : በጎ : ሥርዓት : ለብዙ : ዘ



መን : ፈረሰች : ተናቀችም : ተለወጠችም :: እውነት : ያል
ሆነውን : ታሪክና : ጨወታ : ከብዙ : ምላሽ : አንቀጽም :
ከንቱ : ድጋምም : ተዝካርም : ስኖደስም : ጋራ : አግብተ
ውባታልና : ብዙ : ጊዜ : ከመጽሐፍ : ቅዱስ : አንዱን : መጽ
ሐፍ : ጀምረው : ሶስት : ወይስ : አራት : ምዕራፍ : ከተነበ
በ : በኋላ : የቀረ : ሁሉ : ሳይደገም : ቀረ :: እንዲሁም : የ
ኢሳይያስ : መጽሐፍ : በመምጻት : ጊዜ : የኦሪት : ዘፍጥ
ረትም : መጽሐፍ : በሶስተኛ : እሁድ : በጾም : አርበዒ : በ
ፊት : ተጀመረ : ደሮ : እሌህ : ተጀመሩ : ብቻ : መንበባቸው
ም : ከቶ : አልተጨረሰም :: እንደርሳቸውም : የቀሩ : የመ
ጽሐፍ : ቅዱስ : መጻሕፍት : ሁሉ :: ቅዱስ : ጳውሎስም :
ሌላውን : ቋንቋ : ሰው : ሁሉ : የሚያውቅበት : የሚረባ
በትም : እንጅ : ወደ : ቤተ : ክርስቲያን : እንዲያገቡ : ያዛ
ልና :: በዚች : ግን : በንግልጣር : ቤተ : ክርስቲያን : ለብዙ :
ዘመናት : የማምለክ : ሥርዓት : ሁሉ : ሕዝብ : ባልሰማ
ው : በላቲና : ቋንቋ : ተነበበ : እንዲሁም : በጆሮቻቸው : ብ
ቻ : ሰሙ : ልባቸው : ግን : ነፍሳቸውም : መንፈሳቸውም :
አልተሠራበትም : አልተጠቀመበትምም :: ደግሞም : የድ
ሮ : አባቶች : መዝሙራትን : ሁሉ : በሰባት : ክፍል : ከፈ
ልዋቸው : ክፍሉን : ሁሉን : ሌሊተኛውን : ያልዋቸው :: አ
ሁን : ግን : ከብዙ : ዘመን : ጀምሮ : ከመዝሙራት : ጥቂት :
ብቻ : ተነበቡ : የቀሩም : ፈጽመው : አልተነበቡም :: ደግ
ሞም : ጳይ : ወይስ : ድርጫት : የሚሉት : ሥርዓት : ብርታ
ትዋ : የማገልገልም : ብዙ : መለዋወጥ : መክንያት : ሆነ :
የመጽሐፍ : መገልበጥ : ብቻ : እንዲህ : እንደስቸገረ : የሚ
ደገመውን : ለማገኘት : የተገኘውን : ከመድገም : ይልቅ :
እጅግ : እጅግ : እስኪያስጨንቅ ::
ይህነንም : መከራ : አይተናልና : የሚያበጀውን : ሥር
ዓት : ከዚህ : እነሆ : ሰጠነ :: ይህም : እንደይቸግር : ከለን
ደርዩም : የሚባል : የቀንን : መቍጠርያ : አደረግነ : እር
ሱም : ለማስተዋል : ቃሊል : ነውና : አያስጨንቅም :: በር
ሱም : የመጽሐፍ : ቅዱስ : ማንበብ : በሥርዓት : እንዲህ :

እንደ ፡ ቅሎታችን ፡ ተሠራች ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሥርዓት ፡ እንዲሆን ፡ ክፍልም ፡ ከክፍል ፡ እንዳይቈረጥ ። ለዚህ ፡ መክንያትም ፡ ብዙ ፡ የዜማ ፡ ነገር ፡ አንቲፎኒያ ፡ ርስጶንሶርያም ፡ ኢንቢተተርያም ፡ የሚባሉ ፡ ተቈረጡ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ደህና ፡ መንበብ ፡ እንዳይጉደበት ።

ደሮ ፡ አያሌ ፡ ሥርዓት ፡ ባይኖር ፡ በግድ ፡ አንዳች ፡ አይጠቅምምና ፡ ከዚህ ፡ አንዳንድ ፡ ሥርዓት ፡ ተሰጠች ፡ እርስዋም ፡ እጅግ ፡ አይደለችምና ፡ ቀንታለች ፡ ቶሎም ፡ ያስታውልዋታል ። እንዲሁም ፡ እነሆ ፡ ለጸሎት ፡ ለቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ንባብም ፡ ሥርዓትን ፡ አደረግኒ ፡ እርስዋም ፡ ከድሮ ፡ አባቶች ፡ ፈቃድ ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ ትሰማማለች ፡ በፊትም ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ከሆነች ፡ ሥርዓት ፡ እጅግ ፡ ትሻላለች ፡ ክርስዋም ፡ ይልቅ ፡ ትጠቅማለች ። በዚያች ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ነበረና ፡ ክርሱ ፡ አያሌ ፡ እውነት ፡ ያልሆነ ፡ ያያሌም ፡ እውነት ፡ ተጠራጠረበት ፡ አያሌም ፡ ከንቱ ፡ ወደ ፡ አሰተኛ ፡ መታመን ፡ የሚወስደው ፡ ነገር ። ይህም ፡ ከዚህ ፡ ተቈረጠ ፡ ለማንበብም ፡ አንዳች ፡ አልተሠራም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥሬ ፡ ቃል ፡ እንጂ ፡ ክርሱም ፡ ጋራ ፡ የሚገጥም ፡ ደሀውም ፡ ላንባቦችና ፡ ለሰሞች ፡ ማስተዋል ፡ የዋህና ፡ ቃሊል ፡ ባለ ፡ ቋንቋና ፡ ሥርዓት ፡ ሆነ ። ደግሞም ፡ አይቸግርም ፡ አጭር ፡ ነውና ፡ ሥርዓቱም ፡ ክፍትና ፡ ጽሩ ፡ ናት ፡ ቃኖኖችም ፡ ጥቂትና ፡ ቃሊል ፡ ናቸው ።

በዚች ፡ መንግሥት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ ለመድገምና ፡ ለመዝመር ፡ በፊት ፡ እጅግ ፡ ልዩነት ፡ ነበረች ፡ አያሌ ፡ የሳልስብሪን ፡ ልማድ ፡ አያሌም ፡ የሂርፎርድን ፡ ሌሎችም ፡ የባንገርን ፡ ሌሎችም ፡ የዮርክን ፡ ሌሎችም ፡ የሊንክልንን ፡ ልማድ ፡ ተከተሉ ። ከንጊዴህ ፡ ወዴህ ፡ ግን ፡ ለመንግሥት ፡ ሁሉ ፡ አንዲት ፡ ልማድ ፡ ብቻ ፡ ትሁን ።

ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ በጎና ፡ ቀንታ ፡ እንኳ ፡ ብትሆን ፡ ሰው ፡ ቢያደርጋት ፡ ቢለምደትም ፡ ከቶ ፡ ጥርጣሬ ፡ ሳይነሣ ፡ አይቀርምና ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ማስተዋል ፡ ስለ ፡ ማድረጉም ፡ ስለ ፡ መፈጸሙም ፡



ጥርጣሬ ፡ ቢነሣ ፡ የሚጠራጠር ፡ ሰው ፡ ልቡን ፡ ለማሳረፍ ፡ ወትሮ ፡ ወደ ፡ ግዛት ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይድረስ ፡ እርሱም ፡ በጥበቡ ፡ ጥርጣሬውን ፡ ሁሉን ፡ ለመፍታትና ፡ ለማቅናት ፡ ይድከም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ካለው ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ የሚጸላውን ፡ አንዳችን ፡ እንዲያዝ ፡ ተጠንቀቀ ። የግዛትም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለራሱ ፡ ቢጠራጠር ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ጳጳስ ፡ ጥርጣሬዩን ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ ለምኖ ፡ ይስደድ ።

---

በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያለ ፡ ንባብና ፡ መዝሙር ፡ ሁሉ ፡ በንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡* ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ታዝዋል ፡ ጉባኤው ፡ ትሠራበት ፡ ዘንድ ። ሰዎች ፡ ግን ፡ ለብቻቸው ፡ ኑረው ፡ የጽዋትንና ፡ የማታን ፡ ጸሎት ፡ ቢጸልዩ ፡ እርሳቸው ፡ በሚያውቁ ፡ ቋንቋ ፡ ሁሉ ፡ ቢያደርጉት ፡ ምንም ፡ አይልም ።

ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናትም ፡ ሁሉ ፡ በበሽታ ፡ ወይስ ፡ በሌላ ፡ መክንያት ፡ በግድ ፡ ካልተከለከሉ ፡ የጽዋትንና ፡ የማታን ፡ ጸሎት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ያንብቡ ፡ በግልጽ ፡ ቢሆን ፡ ለብቻቸውም ፡ ቢሆን ።

ባገርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሌላም ፡ በማምለክ ፡ ስፍራ ፡ የሚያገለግል ፡ ቄስ ፡ ሁሉ ፡ በቤቱ ፡ ቢገኝ ፡ በደህና ፡ መክንያትም ፡ ባይከለከል ፡ የዕለት ፡ ዕለትን ፡ ጸሎት ፡ በሚያገለግልባት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያንብበው ፡ ሳይጀምርም ፡ ደወሉን ፡ ያስወዝወዝ ፡ ጉባኤ ፡ ሰምተው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ለመስማት ፡ ክርሱም ፡ ጋራ ፡ ለመጸለይ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ።

---

## ስለ ፡ ሥርዓት ፡ ሜደዊ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ አያሌ ፡ ተሻረ ፡ አያሌም ፡ ቀረ ።

በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከተለመደ ፡ በሰው ፡ ሥርዓትም ፡ ከተጀመረ ፡ ሜደዊ ፡ ነገር ፡ አያሌ ፡ በመጀመርያ ፡ ከደህና ፡

---

* እርስዋ ፡ የንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ቋንቋ ፡ ናትና ፡ የእንግሊዞች ፡ ሕዝብ ፡ የሚያውቁባት ፡ ቋንቋ ።

መክንያት ፡ ተነሣና ፡ ገባ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለከንቱ ፡ ነገር ፡ ላሰ
ተኛ ፡ መታመንም ፡ ተደረገ ። ሌላም ፡ ካለማስተዋል ፡ ዕው
ቀትም ፡ ከሌለበት ፡ መጋደል ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ ገባ ፡ በመጀመርያም ፡ ቅል ፡ ተብልዋልና ፡ አ.የ
ሔደ ፡ ከፋ ፡ እጅግም ፡ ጐዳ ። እንዲህም ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አይ
ጠቅምምና ፡ ሕዝብንም ፡ እጅግ ፡ አሳውርዋልና ፡ የእግዚ
አብሔርንም ፡ ክብር ፡ ከልክልዋልና ፡ ይኸር ፡ ዘንድ ፡ ፈጽ
ሞም ፡ ይጣል ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ። ሌላም ፡ ሚደዊ ፡ ነገር ፡
አለ ፡ ከሰው ፡ ዘንድ ፡ መነሣቱ ፡ ሳይቀር ፡ መኖሩ ፡ ደህና ፡
ሁኖ ፡ የሚመስል ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደህና ፡ ሥርዓት ፡
(ከመጀመርያ ፡ ጀምሮ ፡ ለዚህ ፡ መክንያት ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡)
ለመሥራትም ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ቅዱስ ፡ ሐዋርያም ፡ በቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ የሚደረግ ፡ ሁሉ ፡ ለመሥራት ፡ ይድረስ ፡
ብሎ ፡ ያዘናልና ።

እንዲህም ፡ ያለ ፡ ሚደዊ ፡ ነገር ፡ ቢጠበቅ ፡ ባይጠበቅም ፡
ለራሱስ ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የጉባኤ ፡ ሥርዓት
ና ፡ ተግሣጽ ፡ በፈቃድና ፡ በምቀኝነት ፡ መተላለፉና ፡ ማፍረ
ሱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ታናሽ ፡ መበደል ፡ አይደለም ።
"በመካከላችሁ ፡ የሚደረግ ፡ ሁሉ ፡ በውቀትና ፡ በሥርዓት ፡
ይደረግ" ፡ ይላል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ። የሥርዓትም ፡ መሥራ
ት ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ኢየራሱ ፡ አይገባምና ፡ ማንም ፡ በሕግ ፡
ካልተጸራ ፡ ሥልጣንንም ፡ ካልተቀበለ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ያለቸውን ፡ የጉባኤውን ፡ ሥርዓት ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ወይ
ስ ፡ ይለውጥ ፡ ዘንድ ፡ አይድፈር ።

በዚህ ፡ ዘመኖችንም ፡ የሰው ፡ ልብ ፡ እጅግ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ነው ። አያሌ ፡ ላባቶቻቸው ፡ ልማድ ፡ እንዲህ ፡ ይጠጋሉ ፡ በ
ማምለካቸው ፡ ሚደዊ ፡ ነገር ፡ ጥቂት ፡ እንኳ ፡ መቅረት ፡
ታላቅና ፡ ከቢድ ፡ ነገርን ፡ እንዲቈጥሩ ። ሌሎችም ፡ እንዲ
ህ ፡ ያዲስ ፡ ነገር ፡ ወዳጆች ፡ ናቸው ፡ ነገሩን ፡ ሁሉን ፡ ማደስ ፡
እንዲወዱ ፡ አሮጌውንም ፡ እንዲህ ፡ ይንቃሉ ፡ ከቶ ፡ አንዲ
ቸ ፡ እንደያጸግባቸው ፡ አዲስ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ እንጂ ። ስለዚ
ህም ፡ እኛ ፡ እሌህን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገን ፡ ደስ ፡ እናሰኛቸው ፡



ዘንድ ፡ አልሻነም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ እናሰኝ ፡ ዘንድ ፡
እንጂ ፡ ለሁለታቸውም ፡ እንጠቅም ፡ ዘንድ ። ደህና ፡ መክ
ንያትንም ፡ የሚወደውን ፡ እንደንበድለው ፡ ብለን ፡ ከዚህ ፡
እነሆ ፡ አንደንደን ፡ መክንያት ፡ እንገልጻለን ፡ ከተለመደ ፡
ሚደዊ ፡ ነገር ፡ አያሌ ፡ ስለ ፡ ተሻረ ፡ አያሌም ፡ ቀርቶ ፡ ስለ ፡
ሚጠብቅ ።

አያሌ ፡ ተሻረ ፡ በዚህ ፡ በኋለኛ ፡ ዘመናችን ፡ ብዛቱ ፡ እን
ዲህ ፡ ታላቅ ፡ ሁንዋልና ፡ ሸክሙ ፡ እንደይቻል ። ቅዱስ ፡ አው
ጉሥቲኑስ ፡ በዘመኑ ፡ እንኳ ፡ ተጻደፎ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። የ
ማምለክ ፡ ሚደዊ ፡ ወግ ፡ እንዲህ ፡ ብዙ ፡ ሆነ ፡ የክርስቲያ
ን ፡ ሕዝብ ፡ ንብረት ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ካይሁድ ፡ ንብረት ፡ የከ
ፋ ፡ ሆነ ። እርሱም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ቀምበርና ፡ ሸክም ፡ በ
ዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ደርቅ ፡ ዘንድ ፡ መከረ ። ደሮ ፡ ቅዱስ ፡ አው
ጉሥቲኑስ ፡ አሁን ፡ ባለፈ ፡ ዘምን ፡ በመካከላችን ፡ የነበረ
ውን ፡ የሚደዊን ፡ ወግ ፡ ብዛት ፡ በዘመኑ ፡ ከነበረ ፡ እጅግ ፡
ከበዛ ፡ ባየ ፡ ምንድር ፡ ባለ ፡ ነበረ ፡ ይመስላል ። ይህች ፡ የ
ሚደዊ ፡ ወጋችን ፡ ብዛት ፡ እንዲህ ፡ ታላቅ ፡ ነበረ ፡ ከርሱ
ም ፡ ብዙ ፡ እንዲህ ፡ በምሥጢር ፡ ተሸሽጎ ፡ ነበር ፡ ክርስቶ
ስ ፡ ያደረገልነውን ፡ በረከት ፡ እንደይገልጽልን ፡ ይገሉብጠ
ውና ፡ ያስጨልመውብን ፡ ነበረ ፡ እንጂ ። ደግሞ ፡ የክርስቶ
ስ ፡ ወንጌል ፡ የሚደዊ ፡ ነገር ፡ ሕግ ፡ አይደለም ፡ የሙሴ ፡ ሕ
ግ ፡ እንደ ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለመገዛት ፡
የተሠራ ፡ አምልኮ ፡ ነው ፡ በምሳሌና ፡ በጽላ ፡ ግርነት ፡ ለ
መገዛት ፡ አይደለም ፡ በመንፈስ ፡ አርነት ፡ እንጂ ። እርሱ
ም ፡ ሚደዊ ፡ ነገርን ፡ አይሻም ፡ ለደህና ፡ ሥርዓትና ፡ ለሚ
ጠቅም ፡ ተግሣጽ ፡ የሚገባ ፡ እንጂ ፡ የሰውንም ፡ የደነዘዘው
ን ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚገባውን ፡ አገባብ ፡ አሳ
ስቦት ፡ የሚያስነሣ ፡ በሚገባ ፡ ደህና ፡ ማለትም ፡ ባለው ፡
ምልክት ፡ የሰው ፡ ልብ ፡ የሚሠራበት ። ከዚህም ፡ ጋራ ፡
ሌላ ፡ ታላቅ ፡ መክንያት ፡ ይህ ፡ ነበረ ። ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡
ሚደዊ ፡ ነገር ፡ ተከፍሎ ፡ ባልተማሩ ፡ ሕዝብ ፡ ዕውርነት ፡ ተ
ከፍሎም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ይልቅ ፡ የራሳቸውን ፡

